# <u>ኢ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21-28/2018 የነበረው</u>


# <u>የአየር ሁኔታ ግምገማ</u>

ባለፉት የፌብርዋሪ ስምንት ቀናት ለወቅቱ ዝናብ መኖር አመቺ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ክስተቶች ከዕለት ዕለት በመጠናከራቸዉ አብዛኛዎቹ የበልግ አብቃይ አካባቢዎች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ አግኝተዋል፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ስፍራዎች ላይ አልፎ አልፎ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል። በአጠቃላይ ባለፉት ስምንት ቀናት አብዛኛው ኦሮሚያ፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል፣ ምሥራቅ ትግራይ፣ ምሥራቅ አማራ፣ ጋምቤላ እና ሱማሌ በተለያዩ ቦታዎቻቸው ላይ የተለያየ መጠን ያለዉ ዝናብ መዝግበዋል፡፡ ከባድ ዝናብ ከመዘገቡ ጣቢያዎች መካከል ለመጥቀስ ያህል በጊኒር 39.0፣ በአርጆ 36.4፣ በሆሳዕና 30.5፣ በጂንካ 46.2 እንዲሁም በጃራ 39.5 ሚ.ሜ ሚደርስ ከባድ ዝናብ ተመዝግቧል።


ባለፉት ስምንት ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ የቦታ ሽፋን አንጻር ሲገመገም ከ25-75 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከአማራ ሰሜን ሸዋ፤ ከኦሮሚያ ጅማ፣ ቄለም ወለጋ፣ ኢሉአባቦራ፣ አርሲና ባሌ፣ እንዲሁም ጉጂና ቦረና፤ የደቡብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ ከ4-7 ቀናት ያህል ያህል የዘነበ ሲሆን፤ በተጨማሪም ደቡብ ትግራይ፤ ከጋምቤላ ዞን 1ና 3፤ ከአማራ ሰሜንና ደቡብ ወሎ እንዲሁም ምስራቅ ጎጃም፤ ከኦሮሚያ የሸዋ ዞኖች፣ ምስራቅና ምዕራብ ሀረርጌ አዲስ አበባን ጨምሮ፤ ከሶማሌ የፌቅና የደገሀቡር ዞኖች እንዲሁም ድሬዳዋና ሐረሪ ከ5-25 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ 2-4 ቀናት ያህል አግኝተዋል (ካርታ 1 እና 2) ።

ባለፉት ስምንት ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነጻጸር ከትግራይ የደቡብና የመካከለኛው ትግራይ ኪስ ቦታዎች፤ ከአማራ የደቡብና ሰሜን ጎንደር ኪስ ቦታዎች፣ ደቡብ ወሎ ሰሜን ሸዋ፣ ምስራቅ ጎጃም እንዲሁም የዋግህምራ ዞኖች፤ አብዛኛው ኦሮሚያ፤አዲስ አበባ፤ የደቡብ ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል፤ የጋምቤላ ዞን 1፤ ከሶማሌ የደገሀቡር ዞኖች እንዲሁም ሐረሪ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ ዝናብ የነበራቸው ሲሆን፤ የተቀሩት የሀገሪቱ ክፍሎች ደግሞ ከመደበኛው በታች የሆነ ዝናብ አግኝተዋል (ካርታ 3) ።


ካርታ 1  እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ 2  እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከፌብሪዋሪ 21 እስከ 28 /2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# <u>እ.ኤ.አ  ከፌብርዋሪ 21-28/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

## <u>በግብርናው ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ</u>

ባለፉት ስምንት ቀናት ከላይ በተገለፀው የአየር ሁኔታ ግምገማ መሰረት በአብዛኛው የበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት የበልግ እርሻን ቀደም ብለው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅትና ለዘር ጊዜ የእርሻ ስራ እንቅስቃሴ የተገኘውን እርጥበት በማሳቸው ላይ በማቆየት ለሚጠቀሙት አካባቢዎች ጥሩ አጋጣሚ እንደነበረ ይታመናል። እንዲሁም ከላይ በተጠቀሱት አካባቢዎች ለሚገኙ አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደሮች ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት የጎላ ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ።


ካርታ 4    እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 21 እስከ 28/2016 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



# እ.ኤ.አ ከፈብሪዋሪ 21-28/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

እ.ኤ.አ 21-28 ፈብሪዋሪ 2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረውን ተፅዕኖ ስንመለከት ጥቂት መካከለኛው አባይ፣ መካከለኛውና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞ ጊቤ ከፍተኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛውና የአባይ ደቡባዊው ክፍል፣ የላይኛው አዋሽ፣ ስምጥ ሸለቆ፣ ኦሞጊቤና ዋቢሸበሌ እንዲሁም አብዛኛው ገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት ያገኙ ሲሆን፤ የተቀሩት ተፋሰሶች ከከፊል ደረቅ እስከ ደረቃማ ሁኔታ ላይ ሰንብተዋል፡፡ ይህም ሁኔታ ለበልግ ተጠቃሚ አካባቢዎች አዎንታዊ ሁኔታ እንደነበረው ማረጋገጥ ይቻላል (ካርታ 5)፡፡

ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከፌብሬዋሪ 21 እስከ 28/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ



## .ኤ.አ ከማርች 1-10/2018 የሚኖረው
## የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በማርች የመጀመሪያው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከዕለት ወደ ዕለት እንፃራዊ መጠናከር እያሳዩ በመሄድ የወቅቱ ዝናብ በበልግ አብቃይ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እየተስፋፋና እየተጠናከረ ይመጣል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ከእለት ወደ እለት እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ ከመጠበቃቸው ጋር ተያይዞ በተለይም በበልግ አብቃይ ሥፍራዎች ላይ ዝናቡ ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከኦሮሚያ ክልል ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ምሥራቅ ወለጋ፣ሰሜን ሸዋ፣ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣የቦረናና የጉጂ እንዲሁም ጥቂት የአርሲና የባሌ ዞኖች፤አዲስ አበባ፤ድሬዳዋና ሐረርጌ፤ ከትግራይ የምሥራቅና የደቡብ ዞኖች፤ከአፋር ዞን 3 እና 5፤ ከሶማሌ ክልል ጅጅጋና ሽንሌ፤ ከአማራ ክልል ሰሜንና ደቡብ ወሎ፣ሰሜን ሸዋ፣ምሥራቅ ጎጃም እንዲሁም ደቡብ ጎንደር፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ሁሉም ዞኖች ዝናብ ይኖራቸዋል። በተጨማሪም ከሚጠናከሩ የደመና ክምችቶች በጥቂት ቦታዎቻቸውም ላይ ከባድ ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ አካባቢዎች በአመዛኙ ደረቅ ሆነው ይሰነብታሉ።

## እ. ኤ. አ ከማርች 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

ከላይ በተሰጠው ትንበያ መሰረት በሚቀጥሉት አስር ቀናት በኦሮሚያ፣ በሶማሌ፣ በአማራ፣ በትግራይና በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል በአንዳንድ ዞኖቻቸው ላይ ዝናብ እንደሚያገኙ ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ ለበልግ አብቃይ ለሆኑት አከባቢዎች ለበልግ እርሻ ሥራ እንቅስቃሴዎች አወንታዊ ተፅዕኖ እንደሚኖረው ይጠበቃል፡፡ በመሆኑም የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላትና አርሶ አደሩ ለበልግ እርሻ የማሳ ዝግጅትና የዘር መዝራት ሥራዎችን አጠናክረው እንዲቀጥሉ ይመከራል፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩ

የደመና ክምችቶች በጥቂት ቦታዎቻቸው ላይ ከባድ ዝናብ ሊኖር ስለሚችል የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን እንዲያከናወኑ ይመከራል፡፡

## <u>እ. ኤ. አ ከማርች 1-10/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ</u>

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት ውስጥ በውሃው ዘረፍ ላይ የሚኖረው ተፅዕኖ ስንመለከት ከዝናብ ሰጭ ክስተቶችጋር ተያይዞ በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የእርጥበት መጠን እየጨመረ እንደሚሄድ ትንበያዎች ያመለክታሉ፡፡ በመሆኑም የላይኛውና የአባይ ደቡባዊው ክፍል፣ የላይኛው ባሮ አኮቦ፣ የላይኛውና የመካከለኛው ስምጥ ሸለቆ፣ አብዛኛው ኦሞ ጊቤ፣ የላኛውና መካከለኛው አዋሽ እንዲሁም የላይኛው ዋቢ.ሸበሌ መጠነኛ የሆነ የእርጥበት መጠን የሚኖራቸው ሲሆን፣ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቀ ሆነው ይቆያሉ፡፡ በመሆኑ እርጥበት ያለባቸው አካባቢዎች በተቻለ መጠን ወሃ በመያዝ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው፡፡